# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 177 መስከረም 25 2004 ገጽ 1


**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በሽብርተኝነት ስም እየነዛ ያለውን ሽብር አጥብቆ ያወግዛል። መለስ ዜናዊ እና ቀንደኛ ተባባሪዎቹ አሸባሪዎች በመሆናቸው ለፍርድ እንዲቀርቡ ይታገላል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ሽብር ለማስነሳት ይንቀሳቀሳሉ የተባሉ ወጣቶች አሁንም እየታደኑ በመያዝ ላይ መሆናቸውን የደህንነት ምንጮች ገለጡ

በቅርቡ ሰላማዊ ሰልፍ ለመጥራት ሲዘጋጁ የነበሩ 6 ወጣቶች ከተያዙ በሁዋላ፣ የወጣቶቹ ጉዋደኞች ናቸው የተባሉት ሁሉ እየታደኑ በመያዝ ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ሰሞኑን በወያኔ ጸጥታ ሃይል ከተያዙት ወጣቶች መካከል 4ቱ በመገናኛ አካባቢ፣ 2ቱ ደግሞ በመርካቶ እንደተያዙና በ እስር ቤት ከተወሰዱ ቦኋላ በሽብረተኛው የመለስ ዜናዊ የጸጥታ ሰራተኞች እጅግ አሰቃቂ የሆነ ድብደባ እንደተፈጸመባቸው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

ወያኔ አለኝ በሚለው ህገመንግሥት ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እውቅና ከተሰጣቸው መብቶች አንዱ እንደሆነ ቢታወቅም ህገመንግሥቱን ከለላ አድርገው በአደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ወጣቶች ስብስቦ በሽብርተኝነት ሥም እስር ቤት ማጎርና ሂሊናን በሚሰቀጥጥ ጭካኔ በግርፋት ማሰቃዬት ፤ ወያኔ ስልጣን ከያዘ ከ20 አመታት ቦኋላም ቢሆን ጫካ በነበረበት ወቅት ከተጠራመተው የአውሬነት ባህሪው ገና ያልተላቀቀ መሆኑን ያሳያል የሚሉ በርካቶች ናቸው። ወያኔ በብሄር ጥላቻ አእምሮአቸው የቦዘ አባላቱን በገራፊነት ባሰማራባቸው የማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ የታሰሩ እነዚህ እስረኞች እጅግ አሰቃቂ የሆነ ድብደባ እንደተፈጸመባቸውና በሀይል የግንቦት7 አባላት ነን ብላችሁ መስክሩ እየተባሉ እንደሚጠየቁ ከደህንነት አካባቢ የተገኙ መረጃዎች ያጋልጣሉ።

እንዲሁም ወጣቶቹ ዘራቸው እየተሰደበ በእንጨት ላይ ተንጠልጥለውና ተገልብጠው እንደሚገረፉ፣ ምግብ ሳይበሉ እንዲውሉ እንደሚደረጉ፣ በአንድ እግራቸው ለረጅም ሰአት እንዲቆሙ እንደሚገደዱ የደረሰን መረጃ አክሎ አመልክቷል።

በምርመራ እና በድብደባ ወቅት ሁሉም መርማሪዎች ከአንድ ብሄር የመጡ መሆናቸውን የሚናገሩት ምንጮች፣ በጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማሩ የሌሎች ብሄር አባላት በሽብር ተጠርጥረው ከታሰሩት እስረኞች ጋር እንዳይገናኙ ይከለከላሉ ተብሎአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ወያኔ ወደ ጎሬቤት አገር ለሺያጭ ሊያቀርብ ያሰበውን መብራት ጁቡቲ ላይ ሊጀምር እንደሆነ ተገለጸ

ህዝባችን በሳምንት 3 ግዜ ብቻ መብራት በሚያገኝባት ሀገር የአገሪቱ መብራት ሃይል ኩባንያ ለጅቡቲ መንግስት እስከ 200 ሜጋ ዋት የሚደርስ የኤሌክትሪክ ሃይል ለመሸጥ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ታወቀ።

በኢትዮጵያው ሚሊኒየም አከባበር ሥነሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአሁን ቦኋላ ሻማ የሚያበራው ለልዴት ቀን ብቻ ይሆናል ተብሎ በመለስ ዜናዊ የተለመደው የውሸት ተስፋ ቃል የተገባ ቢሆንም ችግሩ እስከዛሬ ተባብሶ እንደቀጠለ ይታወቃል።

በመላው አገሪቱ ያለው ከፍተኛ የሆነ የመብራት ሃይል እጥረት ህዝባችንን ለከፍተኛ እሮሮ እየዳረገው ባለበት በአሁኑ ሰዓት፤ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መብራት ለጎሬቤት አገር አሳልፎ በውጪ ምንዛሪ ለመሸጥ እያደረገ ያለው መሯሯጥ የስልጣን ዕድሜው እንደማይረዝም በመገመት የተገኘውን ገንዘብ ዘርፎ ለመሄድ እንዲያስችለው ታስቦ እንደሆነ የወያኔን ባህሪ የሚከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

ወያኔ ወደጁቡቲ ለመሸጥ እየሰራ ካለው የመብራት ሃይል በኪሎዋት 70 ዶላር ገንዘብ እንደሚያገኝ ስምምነት ላይ መደረሱ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል። የአገሪቱ ዜጎች ከተወለዱበትና ከአያት ቅድሜ አያቶቻቸው ጀምረው ከሚኖሩበት ቀያቸው እየተፈናቀሉ ለአረብና ለ ኤሽያ ቱጃሮች እየተቸበቸበ ካለው ድንግል መሬታችን ሽያጭ እስከዛሬ ምን ያህል ገንዘብ እንደተገኘ በውል የማይገለጸውና ምን ሥራ እየተሰራበት መሆኑ የማይታወቀው ገንዘቡ በአብዛኛው ውጪ አገር በሚገኙ ባንኮች በግለሰብ ሥም ስለሚቀመጡ ነው ተብሎአል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ የሚያካህደውን የሃብት ዘረፋና የአገር ክህዴት ወንጀል ለማስቆም ጠንክሮ መታገል እንደሚኖርበት የግንቦት 7 ድምጽ በተደጋጋሚ ሲዘግብ እንደቆየ ይታወሳል።

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## በመለስ ዜናዊ የሚመራዉ የአሸባሪዉ የወያነኔ ቡድን ፤ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ የሆነዉ ብስራት አማረ በአሜሪካን አገር በስለላ ተግባር ላይ እንደሚገኝ ተጋለጠ`

ህወሀትን ከተቀላቀለበት ከ1968 ዓመተምህረት ጀምሮ በተሰጠው የአፈናና የግድያ አስተባባሪነት ቦታ በትንሹ ከ 10 ሺህ በላይ ሰዎችን በአሰቃቂ ሁኔታ የገደለውና ያስገደለው ብስራት አማረ ዛሬ ደግሞ አሜሪካ ተመድቦ ውጪ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ እየሰለለ እንደሚገኝ አቶ ገብረመድህን አርአያ አጋለጡ።

ቅጥረኛዉ ነፍሰ ገዳይ ብስራት አማረ፤ አክሱም ተወልዶና እስከ ዘጠነኛ ክፍል ድረስ እዚያው ከተማረ በሁዋላ ህወሀትን መቀላቀሉን የጠቀሱት አቶ ገብረመድህን፤ ”ህንፍሽፍሽ”ተብሎ ከሚጠራውና በአመራሩ ላይ ጥያቄ ያነሱ በርካታ የህወሀት ታጋዮች ከተገደሉበት ጊዜ አንስቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከአረመኔዉ መለስ የሚወጡ የግድያ ትዕዞችን በዋነኝነት ሲፈፅምና ሲያስፈፅም የነበረ በደም የተበከለ ግለሰብ መሆኑን አለኝ የሚሉትን መረጃ በመዘርዘር አጋልጠዋል።

ህወሃት በትግራይ በረሃ ውስጥ ትግል ላይ በነበረበት ወቅት ብስራት አማረና ጓደኞቹ፤ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን በማሰር ጉድጓድ ካስቆፈሩዋቸው በሁዋላ በአንድ ጊዜ በጥይት ደብድበው በመግደል እዚያው ባስቆፈሯቸው ጉድጓድ ውስጥ እንደቀበሯቸው በሀዘን ያስታወሱት አቶ ገብረመድህን፤በጋለ ብረት እየተተኮሱና የፈላ ውሀ እየተደፋባቸው በሚዘገንን ሁኔታ እየተሰቃዩና እየጮኹ የሞቱም ጥቂት እንዳልሆኑ አውስተዋል። የሚገደሉት ሴቶች ከሆኑ ደግሞ ፤በነ ብስራት አማረ የአስገድዶ መድፈር ድርጊት ይፈፀምባቸው እንደነበርም አቶ ገብረመድህን ጠቁመዋል።

አቶ ገብረመድህን፤ በነፍሰ ገዳዮቹ በነ ብስራት አማረ ከተገደሉት ሰዎች የተወሰኑትን በዝርዝር ያቀረቡበትን ይህን ፅሁፍ ያነበቡ ሁሉ፤- “ ጽሁፉ፣አሁን በስልጣን ላይ ያሉት የህወሀት ቁንጮዎች ገና ከመነሻው ጀምሮ ምን ዓይነት ጨካኝና ደም መጣጭ ሰዎች መሆናቸውን ያመላከተን ነው” ሲሉ አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በሎንዶንና በኦስሎ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚዎችን በሽብርተኝነት እየፈረጀ ማሰሩን በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ

የሥልጣን ዘመኑን እስከወዲያኛው ለማራዘም የሚችል መስሎት የሚቃወሙትን ሁሉ በሽብርተኝነት እየፈረጀ ዘጎችን ወደ እስር ቤት ማጎር የጀመረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያለአገባብ እያሰቃያቸው ያለውን ወገኖቻችንን እንዲፈታ ለመጠየቅ በ እንግሊዝና በኖርዌዩ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ባለፈው አርብና እሁድ በየሚኖሩባቸው አገሮች ዋና ከተሞች በሎንዶንና ኦስሎ ሰልማዊ ሰልፍ ማድረጋቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢዎች ባስተላለፉት ዜና ገለጹ።

መለስ ዜናዊ ሽብርተኛ ነው፤ መለስ ዜናዊ ፋሽስት ነው፤ መለስ ለፍርድ ይቅረብ የታሰሩት ጋዜጦኞች በመሉ ይፈቱ ወዘተ የሚሉ መፈክሮችን ያነገቡ የሁሉቱም አገር ሰልፈኞች በኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ በወያኔ ፋሽስታዊ አገዛዝ እየተፈጸመ ነው የሚሉትን በደሎች በመዘርዘር ለየሚኖሩባቸው አገሮች መንግሥታዊ ተቋሞችና ፓርላማ አባላት በጽሁፍ አቅርበዋል።

በኖርዌይ ሰላማዊ ሰልፉን ያስተባበሩት ኢትዮጵያዊያን ተወካይ ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለተገኙት አገር ወዳዶች ባደረጉት ንግግር ወያኔ ወገኖቻችን ላይ ጥቃት ባደረሰ ቁጥር ሰላማዊ ሰልፍ አዘጋጅቶ ማውገዝ ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ገልጸው፤ ይልቁንም “የችግራችን ምንጭ የሆነውን ይህንን ዘረኛ አገዛዝ ከሥልጣን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ እያንዳንዳችን ጉልህ ድርሻ መጫወት ይኖርብናል” ብለዋል። አያይዘውም “ሁላችንም በሚመስለንና አላማውና ፕሮግራሙ ከምንጋራው ድርጅት ጋር ተቀላቅለን ለነጻነታችን ለሚደረገው ትግል አስተዋጾ ማድረግ ይጠበቅብናል ፤ በትግሉ ሂዴት የወያኔ ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችንንና ቤተሰቦቻቸውንም በገንዘብና በማቴሪያል ለመደገፍ ከጎናቸው መቆም ግዴታችን መሆን ይኖርበታል” ብለዋል። በመጨረሻም “መለስ ዜናዊ የፊታችን ሰኞ መስከረም 29 በኦስሎ በሚያደርገው ግብኝት ነፍሰ ገዳይነቱንና ሽብርተኝነቱን በጋበዙት ምዕራባዊያን አጋሮቹ ፊት ለማጋለጥ እንድንችል ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ እያዘጋጀን ስለሆነ ሁላችሁም በዚያ ስልፍ ላይ በመገኘት ወገናዊነታችሁን እንድትገልጹ ጥሪ እናቀርባለን” በማለት ንግግራቸውን አጠናቀዋል። በሰልፉ ላይ የተገኙት ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆችም ቀደም ሲል ያራ የተባለው የማዳበሪያ አምራች ድርጅት ለዘረኛው መለስ ዜናዊ በኦስሎ ከተማ ላይ አዘጋጅቶ በነበረው የገንዘብ ሽልማት ላይ ተገኝተው ዘረኛውን የወያኔ ቁንጮ እንዳዋረዱ ሁሉ በፈረንጆች አቆጣጠር አክቶበር 10 ለሚደረገው ስልፍ ተዘጋጅተው እንደሚጠብቁት በመዛት ፕሮጋራማቸውን አጠናቀዋል። ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የሽብርተኝነት ትርጓሜዎች ሲዛቡ

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ “ሽብርተኛ” የሚለው ቃል ትርጉሙ ተዛብቷል። በአገራችን ሰዎች “ሽብርተኝነትን” ቢያንስ በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ይረዱታል።

1. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ “በአሸባሪነት” “ጠርጥሮ” ያሰራቸውን ዜጎችን ስብዕና ያስተዋሉ፤ “ሽብርተኛ” የጨዋነት፣ የመልካም ሥነ-ምግባርና የመልካም ዜግነት መጠሪያ አድርገው ወስደውታል። እናቶች ልጆቻቸው ሲያድጉ እንደ አቶ አንዱዓለምና አራጌ፣ እንደ አቶ እስክንድር ነጋ ወይም እንደ ወ/ት ርዕዮት ዓለሙ ስም አስጠሪ እንዲሆኑላቸው ይመኛሉ። ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ መታገል፤ ሃሳብን በነፃ መግለጽ፤ ነፃነትንና ፍትህን መስበክ .... ሽብርተኛ የሚያስብሉ ከሆነ “እኔም አሸባሪ ነኝ!” የሚሉ ድምፆች ከየአቅጣጫው እየተሰሙ ነው፤ በጽሁፍም እየቀረቡ ነው።
2. “የፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል” እየተባለ የሚንቀለጳጳሰው አካል የሚያወጣቸው መግለጫዎችና የሚያሰራቸው “ዶክመንተሪ” ፊልሞችን የተከታተሉ ሰዎች “ሽብርተኛ” ማለት የቀልድ ልብ-ወለድ ገፀ-ባህሪ አድርገው ወስደውታል። በዚህም ምክንያት ደራሲዎቻቸው የማይታወቁ በርካታ “ሽብርተኛ” ቀልዶች ሰውን ያዝናናሉ።
3. በሌሎች አገራት “ሽብርተኛ” የሚባሉ ሰዎችን ባህርያትንና ተግባራትን የተከታተሉ ደግሞ የአገራችን ቀንደኛ ሽብረተኞች መለስ ዜናዊ እና ጥቂት ባልደረቦቹ መሆናቸው ይረዳሉ። ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ሽብርተኝነትን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት የመለስን አገዛዝ ማስወገድ ግዴታ እንደሆነ የተገነዘቡ ናቸው።

የሽብርተኝነት ትርጉም እንዲህ ቢምታታም በመለስ ዜናዊ “ሽብርተኛ” መባልና በኢትዮጵያ ህዝብ “ሽብርተኛ” መባል ለየቅል መሆናቸውን ማስረገጥ ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያዊያን ዓይን ሲታይ መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ በሽብር ተጸንሰው፤ በሽብር ያደጉ እኩይ ኃይሎች ናቸው። መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ በኢትዮጵያዊያን ደም ተረማምደው፤ ብዙ ድልድዮችን አፍርሰው እና በርካታ ባንኮችን ዘርፈው ምኒሊክ ቤተመንግሥት መድረሳቸውን እነሱም አይክዱትም። በረሃ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ የተለየ አስተያየት የያዙ፣ አሊያም ወደፊት ይቃወሙን ይሆናል ብለው የጠረጠሯቸውን ወዳጆቻቸውን ሳይቀር ገድለዋል፤ አሰቃይተዋል። ቅልብ ገዳዮችን በማስማራት በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በሻሸመኔ፣ በአሰበ ተፈሪ፣ በሆሮ ጉዱሩ፣ በሀረር፣ በጋምቤላ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ እና በሶማሊያ የጅምላ ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽመዋል።

ቦንቦችን እያፈነዱ ዜጎችን ከገደሉ በኋላ በኦነግና በኦብነግ ሲያላክኩ ኖረዋል። ከአሜሪካ ኤምባሲዎች ሾልከው የወጡ የዊኪሊክስ መረጃዎች እንዳረጋገጡት መለስና ቡድኑ በድብዳባ የሞተን ሰው እንደና በፈንጂ እንዲሞት አድርገው “የሽብርተኛ” ድራማ የሰሩ አጋንንት ናቸው። እነሱ የፈፀሙት የሽብር ሥራ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

በመለስ ዜናዊና ተከታዮቹ ውሸቶች ሌላው ቀርቶ “የፀረ-ሽብር ግብረ-ኃይል” ተብየው ቡድን አባላትን እንኳን ሳይቀር ተንገሽግሸዋል። “ግብረ-ኃይል” ተብዬው የመለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን ቀኝ እጅ በሆነ አንድ ዘረኛ ግለሰብ የሚዘወር መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ቀሪዎቹ አባላት በቡድኑ ስም የሚፈጸመው ሰቆቃ፤ የሚነዛው ፕሮፖጋንዳና ጉራ መልሶ እነሱኑ የሚያጠፋቸው እንደሆነ እየተረዱት ነው።

መለስና ልቦናቸው የታወሩ ወዳጆቹ የማያውቋቸው አሊያም ሊያውቋቸው የማይፈልጓቸው ሃቆች አሉ።

1. ህዝብ የሚሰሩትን ያውቃል፤ በቀልድም በአሽሙርም በዜናቸው ላይ ያፌዛል፤
2. የኢትዮጵያ ህዝብ መለስንና ቡድኑን ለመቅጣት አድብቷል፤
3. የኃያላን መንግሥታት ተወካዮችም የተታለሉ ቢመስልም ውስጥ ውስጡን ግን እየሳቁባቸው ነው። ይህንን ማወቅ የሚፈልግ የዊኪሊክስ መረጃዎች ያንብብ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በሽብርተኝነት ስም እየነዛ ያለውን ሽብር አጥብቆ ያወግዛል። መለስ ዜናዊ እና ቀንደኛ ተባባሪዎቹ አሸባሪዎች በመሆናቸው ለፍርድ እንዲቀርቡ ይታገላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## በአዲስ አበባ ከተማ እየተቀጣጠለ የመጣውን የህዝብ ተቃውሞ ለማምከን በመማር ላይ ያሉ የወያኔ አባላት ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ትዕዛዝ መተላለፉ ተዘገበ። ምክንያት ለምርጫ 2005 ፤ከወዲሁ መሰናዶ ለማድረግ ነው ተባለ።

ወያኔ የአዲስሰ አበባ መስተዳደር በ2005 ዓ.ም. ለሚያደርገው ምርጫ የቅስቀሳ ሥራ እንዲሠሩ በሚል ሰበብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በተለያየ የትምህረት ደረጃ በመጀመርያ ዲግሪና በሁሉተኛ ዲግሪ መርሐ ግብሮች በማመር ላይ የሚገኙ አባላቱን፣ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡና አስፈላጊዉን ቅድመ ምርጫ ዝግጅት እንዲያደረጉ አሳሰበ።

99 ነጥብ 6% ህዝብ መርጦኛል ከኔም ፍቅር አለዉ እያለ የሚመጻደቀዉ የወያኔዉ ዘረኛ አገዛዝ ያዲስ አበባን ህዝብ ቀብሮትም ቢሆን እንደማያምነዉ በሚገልጽ መንገድ በከተማዋ ያሉትን ሆድ አደር ካድሬዎቹን ሰብስቦ ተቃዋሚዎች በ2004 ኢህ አደግን ከሥልጣን እናስወግዳለን በማለት እያደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴ ለማክሸፍ የሞት የሽረት ትግል እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ማስተላለፉ ታወቀ።

ወያኔ ለካድሬዎቹ በሰጠው በዚህ ትዕዛዙ ተቃዋሚዎች 2004ን እንደምርጫ 97ቱ ወቅት የአዲስ አበባን ህዝብ ሙሉ በሙሉ በጸረ ኢህአደግ ዘመቻ ሊያሳትፉ እየተራወጡ ስለሆነ፤ እያንዳንዳችሁ ይህንን ለማክሸፍ በሙሉ ጉልበታችሁና ሃይላችሁ መንቀሳቀስ የግላችሁን ህይወት ለመሻሻል ከጀመራችሁት ትምህርት የበለጠ ዋስትና የሚሰጣችሁ ነው በማለት እያስፈራራ እንደነበረ ለማወቅ ተችሎአል። ት ዕዛዙን የሰጡ ሹሞች ደጋግመው ”ዘንድሮ የሞት የሽረት ዓመት ነዉ፤ ባሁኑ ሏአት በአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ላይ የ97ቱ ዓይነት ስሜታዊ መነቃቃት እየተስተዋለ ነው” በማለት ሲናገሩ ከመሰማታቸው በተጨማሪ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰአት የሚታየውን የህዝብ ብሶት ምሬትና በቃኝ ባየነት አገዛዙን ምን አይነት ፍርሃትና ድንጋጤ ላይ እንደጣለው አመልካች ነው ተብላአል ምንጮች።

ወያኔ በመላው አገሪቱ እያየለ የመጣው ህዝባዊ ጥላቻ በአባላቱ ውስጥ ምን ያህል እንደሰደደ ለማወቅ ካለፈዉ መስከረም 10ቀን ጀምሮ እስከ ትላንት ድረስ ከሚኒስትሮች እስከ የበታች ሠራተኞች የዘለቀ ወያኒያዊ ግምገማ እንዳካሄደ የታወቀ ሲሆን ፤ በዚህም ግምገማ በዋነኛነት «፡"የአመራር ሚናችሁ ምንድነው? በከተማው ውስጥ ቅሬታ የሚያቀርቡ የኅብረተሰብ ክፍሎች በዝተዋል፤" ያዲሳባ የምርጫ ችግር የህልዉናችን ችግር ነዉ ።|» በሚሉ ጉዳዮች ሲብጠላጠሉ ከቆዩ በኋላ ወያኔ የራሱን ዉሳኔም አሳዉቋቸዋል። በዚህመወ መሰረት ፡ በህዝብ ሀብትና ንብረት በየ ዩኒቨሪስቲዎችና ኮሌጆች የሚማሩ ካድሬ አባላቱ በሙሉ ካሁን ጀምሮ እነዚህን 2 ዓመታት ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡና ካድሪያዊ ተግባራቸዉን በትጋት እንዲጀምሩ ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፏል።

ሆኖም ዘጋቢያችን ካነጋገራቸዉ ካድሬዎች እንደተረዳወ ካድሬዎቹ በ እዉነትም ያዲሳባን ህዝብ እንኳን አሁን ነጻነቴ በሚልበት ሰዓት ይቅርና በ97ቱም እናዉቀዋለን ሁሌም በሰቀቀን ነዉ ያለነዉ ስለዚህ «ትምህርታችንን አቋርጠን በምርጫ ብንሸነፍ ምን ልንሆን ነው?" የሚል ጥያቄ እርስ በርሳቸው በማንሳት በከፍተኛ ጭንቀት ላይ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ ድህረ ምርጫ 97 ቁጥራቸውን ወደ 5 ሚሊዮን አድርሶአቸው ከነበሩት አባላቱ መካከል በርካቶችን ለመቀነስ እቅድ እንዳለውና ይህንኑ ለመተግበር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ዘጋቢያችን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ያገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ገልጾአል። ወያኔ የአባላቱን ቁጥር ለመቀነስ የተገደደው፤ በኑሮ ዋጋ መናርና አገዛዙ በሚከተለው ዘረኛ ፖሊሲ ምክንያት “ኢህአደግ” በተባለው ስብስብ ውስጥ የትግራይ የበላይነት የፈጥረው ጥላቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ በመምጣቱ፤ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሳጠር የሚችል ትልቅ አደጋ አዝሎአል ተብሎ በመለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ በመታመኑ እንደሆነ እነዚሁ ምንጮች አክለው መግለጻቸው ታውቆአል።

ወያኔ “ኢህአደግ” በማለት በሚጠራው ድርጅት ውስጥ የተንሰራፋውን የህወሃት የበላይነት የሚቀናቀኑትን በግምገማ ስም ሲመነጥር የኖረ መሆኑ ቢታወቅም፤ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች በአንዴ ማሰናበት ሊያደርስበት የሚችለውን የፖለቲካ ኪሳራ ለመቀነስ የሚያስችለውን ብልሃት አጥንቶ የሚያቀርብ ቡድን መመስረቱን ለአመራሩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ተናግረዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ የትግራይ ክልል ነዋሪዎች በስርአቱ ላይ የሚያሰሙት ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ኢሳት በትናንትናው ዜና እወጃው ዘግቦአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ "ከያዝነው የመስከረም ወር መባቻ ጀምሮ ትግራይ ውስጥ አገዛዙን አይደግፉም፣ ለጸረ ሰላም ሀይሎች መሳሪያ ሆነዋል" የተባሉ ወጣቶች ለእስርና ለወከባ እየተዳረጉ መሆኑ ሲገለጽ፤ ለህወሃት መስመር ተገዢ አልሆናችሁም ተብሎ በአረና ፓርቲ ደጋፊነት እየተፈረጁ ከያሉበት ታድነው ለእስርና ለእንግልት ከተዳረጉት ያመለጡ በርካታ ወጣቶች ወደ በረሃ በመጓዝ የትግራይ ዲሞክራሲ ንቅናቄ በመባል የሚታወቀውንና ወያኔን በትጥቅ ትግል በመፋለም ላይ የሚገኘውን ድርጅት እንደተቀላቀሉ ተዘግቦአል።

## በአንድ ሰው ስሜት የምትገዛ አገር!!!

ከምድር በታች ኢትዮጵዊያንን የሚያስተዳድር አንድ ህግ ብቻ አለ።ይህ ህግ የመለስ ዜናዊ ስሜት ነው። ይህ ስሜት ደግሞ በጫት፤በሲጋራና በመጠጥ ሱሶች የተበከለ ብቻ ሳይሆን ጥልቅ በሆነ ክፋትና ጥላቻ መንፈስ የተሞላ ነው። ይሄም መንፈሱ ጭካኔን፤ ጭካኔውም ፍርሃትን ፈጥሮበት አገራችንን እያሸበራት ይገኛል።

መለስ ዜናዊ ጫቱን ቅሞ ሲያበቃ የራሱ ጥላ ጭምር ግንቦት ሰባትን እየመሰለው ያየውን ሁሉ ያዙልኝ እሰሩልኝ ግደሉልኝ እያለ መቃዥት ከጀመረ ሰንብቷል። መለስ ዜናዊን የሚያቃዠውና የሚያስበረግገው የፍትህ፤ የእኩልነት፤ የህግ የበላይነት፤ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ፤ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ሰው የመሆን ጥያቄዎች የሁሉም ጥያቄዎች ናቸውና መለስና በዙሪያው የተሰበሰቡ ሆዳቸው አምላካቸው ክብራቸው በነውራቸው የሆኑ ጋሻ ጃግሬዎቹን ያሸበሩዋቸዋል።

መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ  ዴሞክራሲያዊ ተቋማት እንዲገነቡ ሲጠየቁ ይሸበራሉ። የእነዚህ ተቋማት በነጻነትና በህግ መቋቋም የመለስ ዜናዊና የግብረ-አበሮቹን ህልውና ከመሰረቱ የሚንድ ነው። የዚህ ቡድን የህልውናው መሠረት የቆመው በዝሪፊያ ነው። ይህን ዝርፊያ የሚጠይቅ፤ የሚከታተልና ሌባውን ለፍርድ የሚያቀርብ አካል እንዲፈጠር የሚጠይቅ አካል ሁሉ በአሸባሪነት ይፈረጃል። ከአገሪቷ ካዝና ውስጥ 8.5 ቢሊዮን ዶላር ወጥቶ በውጭ ባንክ ውስጥ ተደብቆ መቀመጡን የተባበርት መንግስጠታት ከነገረን በኋላ ይሄ እንዴት ሆነ ብሎ የሚጠይቅ አካል አሸባሪ ነው። የአገሪቷን ለም መሬት ለባእዳን አልፎ የተሰጠው እንዴትና በምን ሁኔታ ነው ብሎ መጠየቅ አሸባሪነት ነው። ባገሪቷ ብሄራዊ ባንክ ውስጥ የተቀመጠ ወርቅ በባሌስትራ ተተክቶ ሲገኝ ይሄ እንደምን ሁኖ ተፈጸመ ብሎ መጠየቅ አሸባሪነት ነው። አስር ሺህ ቶን ቡና የደርሰበት ጠፋ ሲባል ገና በአውቶብስ ላይ ሊጠመድ የታሰበን ቦንብ ይዤ አከሸፍኩ የሚለው ቡድን አስር ሺህ ቶን ቡና የገባበትን እንደምን ማወቅ ተሳነው ብሎ መጠየቅ አሸባሪነት ነው። ይህን መሰሉን ወንጀል ማን እንደፈጸመው የሚከታተል ህጋዊና ገለልተኛ አካል ማቋቋም ማለት በገዛ አንገት ላይ ማነቆ ማስገባት ስለሚሆንበት መለስና ቡድኑ በጄ አይሉም። በተግባር ከተገለጡት የመለስ ዜናዊ  አሸባሪ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ እነዚህ  ናቸው።

መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ የህግ የበላይነት ጥያቄ ሲነሳ ይሸበራሉ።መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ ህግን የሡሩት ዜጎችን ለማጥቂያነት ነው እንጂ በአገሪቷ ውስጥ ሥርዓትና እኩልነት እንዲሰፍን አስበው አይደለም። በዚያ ጠባብ ብሄረተኛ አመለካከታቸው ያወጡት ህግ ውስጥ ያልተካተተ ሁኔታ ቢፈጠር እንኳ እድሜ ለጫት በአንዲት ጀንበር ህግ አውጥተው አድረው ዜጎችን ለማንገላታት ይጠቀሙበታል። መለስ ዜናዊ ወደ ዱር ከገባ ጀምሮ ከህግ በላይ ሁኖ ማንኛውንም ዓይነት ወንጀል ሲፈጽም የኖረ ነው።ከብዙ ወንጀሎቹ መካከል ጥቂቶቹን ብቻ እናስታውስ። የሃውዜን ህዝብ ሆን ተብሎ ገበያ እንደወጣ እንዲጨፈጨፍ የተደረገው በመለስ ዜናዊ መሪነት ነው።ለርሃብተኛ የተመጸወተውን ነፍስ አድን እህል በሱዳን ገበያዎች ልኮ አሽጠው የረሃበተኛውን ገንዘብ በግል ባንክ እንዲቀመጥ የተደረገው በመለስ ዜናዊ መሪነት ነው። አባቶችን በህጻናት ልጆቻቸው ፊት ማዋረድና ህጻናቱ የአእምሮ ጭንቀት ውስጥ እንዲወድቁ የሚደረገው በመለስ ዜናዊ መሪነት ነው።ዜጎች ከያሉበት እየተለቀሙ ለመስማት በሚቀፍ ሁኔታበዘራቸው ምክንያት እየተሰደቡ ሰቆቃ እንዲፈጸምባቸው የሚደረገው በመለስ ዜናዊ መሪነት ነው። በሞት አፋፍ ላይ የደረሱ ሩጦ ማምለጥ የማይችሉ ደካማ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ተይዘው የሚገረፉበት ዘመን የመለስ ዜናዊ ዘመን ነው።አሸባሪነት ማለት እንዲህ ዓይነት ነውር ተግባራትን መፈጸም ነው እንጂ የህግ የበላይነት ይከበር ማለት አይደለም።

መለስ ዜናዊና ቡድኑ ነጻ ሚዲያ በአገሪቷ ውስጥ እንዲፈጠር ሲጠየቁ ይሸበራሉ። ዛሬ ጎሬቤታችን ኬኒያ ከአስር በላይ የግል ቴሌቭዥን ጣቢያዎች አሏት። በኬኒያ ምድር መንግስት የሚሰራው ክፍም ሆነ ደግ ነገር ከህዝቡ ተሰውሮ አይቀርም።አንድ ኬንያዊ በራሱ ቋንቋ ከሚተላለፍ ከአስር በላይ የተሌቭዥን ጣቢዎች መካከል ደስ ያሰኘውን መርጦ ማየት ይችላል። ይሄ ግን ለኢትዮጵያዊያን የሚፈቀድ አይደለም። ይሄንንም የጠየቀ ከተገኘ አሸባሪ ተብሎ የእድሜ ልክ እስራት ይጠብቀዋል። የህዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ ለህብረተሰብ እድገት ከፍተኛውን አስተዋጾ የሚያበረክተውን ነጻ ሚዲያ መከልከል ነው እንጂ አሸባሪነት ይሄ እንዲኖር መጠየቅ አይደለም። መለስ ዜናዊና ቡድኑ ነጻ ሚዲያ ቢቋቋም የሰሯት ወንጀል ሁሉ በመረጃ እየተደገፈች አደባባይ መውጣቷን ጠንቅቀው ስለሚረዱ ነጻ ሚዲያ እንዲኖር የሚጠይቀውን ሁሉ በአሸባሪነት ፈርጀው ያስራሉ፤ ሰቆቃ ይፈጽማሉ፤ይገድላሉ። እንዲህም በማድረግ ሽብረተኛ ተግባራቸውን ይገልጣሉ።

መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ ገለልተኛና ነጻ የሆነ የሰብዓዊ መብት ተመልካች ተቋም እንዲኖር ሲጠየቁ ይሸበራሉ።ገለልተኛና ነጻ የሆነ የሰብዓዊ መብት ተመልካች ተቋም ቢቋቋም መንግስት የሚጎዳው ምንም ነገር አልነበረም። እነ መለስ ግን ገለልተኛና ነጻ ተቋም እንዲቋቋም የማይፈልጉት አንድ መንግስት ማሟላት ያለበትን መሠረታዊ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ስለማያሟሉና ሃልፊነት የሚባል ነገር ስለማይሰማቸው ነው። ይሄ ቡድን የሚያወቀው የሰዎችን መብት ረግጦ የፈለገውን እስከሚሰለቸው  ድረስ አስሮ፤በፈለገው ላይ የሞት ፍርድ ፈርዶ፤ ያልፈለገውን ደግሞ በጠራራ ጸሃይ ገድሎና ሜዳ ላይ ጥሎ ሲኖር እንጂ ለሰው ልጆች መብትና ክብር ሲሰራ አይደለም። የሰው ልጆችን ሲገድል ሲያስር ሲያሰቃይ የኖረ ቡድን ገለልተኛና ነጻ የሆነ የሰብዓዊ መብት ተመልካች ተቋም ይቋቋም ሲባል ይሸበራል። ይሄንንም የጠየቀ አካል ከተገኘም አሸባሪ ይባልና የሞት ፍርድ ይፈረድበታል።ይሄም ሌላ የአሸባሪነታቸው ጠባይ መገለጫ መንገድ ነው።

በአጠቃላይ በመለስ ዜናዊ ዘመን ሰብዓዊ መብትና የህግ የበላይነት ይከበር፤ሌባ ለፍርድ ይቅረብ፤ መልካም አስተዳደር ይስፈን፤ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት ይኑሩ፤ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ያለገደብ ይፈቀድ ማለት አሸባሪነት ነው። እነመለስ ዜናዊ እነዚህን መብቶች ገፈው ዜጎችን ከሰው በታች አድርገው ለመግዛት ባላቸው ጽኑ እምነት ዜጎችን እያሸበሩ ይገኛሉ። ይሄን መብት ረገጣ ሽብር እምቢ በማለት በመለስ ዜናዊ "አሸባሪ" መባል የሊሻን ሽልማት ነው። በመለስ ዜናዊ "አሸባሪ" መባል እንደ በላይ ዘለቀና እንደ አብዲሳ አጋ ስመ ጥር አርበኛ መሆን ማለት ነው። በመለስ ዜናዊ አሸባሪ ተብሎ መጠራት እንደ መጽሃፍ ቅዱሱ ሙሴ ከቤተ-መንግስት ምቾት ይልቅ የተገፉና የተበደሉ ወገኖችን ወገኖቼ ብሎ ለእነርሱ ነጻ መውጣት ራስን መስዋእት አድርጎ ማቅረብ ነው። በዚህ ዘመን አሸባሪ መባል መለስ ዜናዊ ላቆመው በዝሪፊያ በዘረኝነትና በወንጀል ስርዓት ውስጥ አልሳተፍም ብሎ ለእውነትና ለፍትህ ጸንቶ መቆም ማለት ነው።በዚህ ዘመን አሸባሪ መባል መለስ ዜናዊ ላቆመው ጣኦታት አልገዛም ለሚሉ ብርቅየ ዜጎች የሚሰጥ የክብር ሽልማት ነው።

ዛሬ የመለስ ዜናዊን የክፋትና የዘረኝነት ሥርዓት በመቃወማቸው አሸባሪ የተባሉት ምርጥ የአገራችንን ልጆች ታሪክ በክብር መዝገቡ ይመዘግባቸዋል። ኢትዮጵያችን ስትፈርስ፤ ለም መሬቶቿ ለባእዳን ተላልፈው ሲሰጡ፤ ዜጎቿ በመከራ ውስጥ በሆኑ ግዜ፤ የሴቶቻችን እንባ እንደ መጽሃፍ ቅዱሷ ራሄል እንባ ጽዋውን ሞልቶ ሲፈስ አይተው  ዝም አላሉምና ስማቸውን ትውልድ ሁሉ በክብር እንዳነሳው ይኖራል።

መጨረሻም በጫት፤ በሲጋራና በመጠጥ ሱስ የናወዘውንና የሰው ደም ያሰከረውን መለስ ዜናዊንና ግብረ-አበሮቹን ከነ-ጣኦቶቻቸው ከኢትዮጵያችን ላይ እንዲነሱ የሚደረገው ትግል በውጭም በውስጥም ተጠናክሮ ይቀጥላል። እነዚህን ወሮ በላዎች ለረዥም ግዜ መሸከም ማለት አገራችንን ለከፋ ውርደት አሳልፎ መስጠት ማለት ነው። እነዚህ ሆዳቸው አምላካቸው ክብራቸው በነውራቸው የሆኑ ፈጣሪ የማያውቁ ሰውንም የማያፍሩ እርባና ቢስ ቡድኖች ከተቆናጠጡት ወንበር ወርደው ፍትህ እንዲነግስ፤ ነጻነት እንዲሰፍን፤እኩልነት እንዲታወጅ፤ የዴሞክራሲ ወጋገን በአገራችን እንዲንጸባረቅ ማድረግ ለራሱ ክብር ከሚሰጥ ዜጋ ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው። በእኛ በኩል የቀረን አማራጭ ይሄው ብቻ ነውና የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን እንጂ ለደቂቃም ቢሆን አንዘናጋም።

**ድል ለኢትዮጵይ ህዝብ ይሁን !!!**

## በመለስ ዜናዊ የሚመራዉ የአሸባሪዉ የወያነኔ ቡድን ፤ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ የሆነዉ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

"ብስራት ዛሬ አሜሪካ መጥቶ በየፓልቶኩ የወያኔን ብፅዕና ሲሰብክና ሲመፃደቅ እየሰማነው ነው" ያሉት አቶ ገብረመድህን፤" ይሁንና፤ እየገረፈና እየገደለ ስለገነባው ድርጅት ጥብቅና ቢቆም ባህሪያዊ ነውና መገረም የለብንም"ብለዋል። አቶ ገብረመድህን አያይዘዉም ህወሀት በትጥቅ ትግሉ ጊዜ በትግራይ ህዝብ ስም ያገኘውን በመቶ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር እርዳታ ፤ ለድርጅቱ እንዳዋለው ተጨባጭ መረጃዎችንና ፎቶግራፎችን ጭምር ዋቢ አድርገው ማጋለጣቸው ይታወሳል።

አቶ ገብረመድህን አረ አያ የህወሃት ፋይናንስ ሃላፊ ሆነው ለበርካታ አመታት ከሰሩ በኋላ የህወሃት አመራር እየያዘ በሄደው የጸረ ኢትዮጵያ አቋም ልዩነት ፈጥረው ከድርጅቱ እንደተለዩና በጊዜው ሥልጣን ላይ ለነበረው ደርግና ሊትዮጵያ ህዝብ እጅግ ጠቃሚ የነበሩ መረጃዎችን ምንም ሳይደብቁ ይፋ አድርገው የነበሩ አገር ወዳድ ሰው እንደሆኑ ይታወቃል። የአቶ ገብረመድህንን መረጃ በአገባቡ ያልተጠቀመው ደርግ እራሱ ወድቆ አገሪቷንም አሁን ካለችበት አደጋ ውስጥ ከቶአት እንዳለፈ ታሪክ በተደጋጋሚ ስገለጽ ኖሮአል።

## ሽብር ለማስነሳት ይንቀሳቀሳሉ የተባሉ ወጣቶች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በወያኔ እስር ቤት ያለው ዘረኛነት ያስመረራቸው እንደነ አቶ ክንፈ ሚካኤል ደበበ የመሳሰሉት ደፋር ፖለቲከኞች ለምርመራ ከተመደቡት ህወሀት መርማሪ ፖሊሶች ጋር እስከ መሰዳደብ መድረሳቸውን፣ ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ይህ በዚህ እንዳለ እነ አርቲስት ደበበ እሸቱ  ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዳይገናኙ መደረጋቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

## የወያኔ ጸጥታ ሃይሎች በደቡብ ኢትዮጵያ የሀዲያና አላባ አካባቢ ነዋሪዎች ላይ በከፈቱት ተኩስ እሩምታ የ4 ንጽሃን ህይወት መቀጠፉንና በርካቶች መቁሰላቸው ተዘገበ

በሃዲያ ዞን የባዳወቾ ወረዳ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የአላባ ብሄረሰብ አባላት የሚኖሩበት አከባቢ በአላባ ልዩ ወረዳ ስር እንዲካለል ቀድም ሲል ያቀረቡት ጥያቄ መልስ ባለማግኘቱ የተነሳ በተፈጠረው ችግር፤ ችግር ፈጣሪ የሆነው የወያኔ ጸጥታ ሰራተኞች በህዝቡ ላይ በከፍቱት የተኩስ እሩምታ ከ20 ሰዎች በላይ በጥይት መመታታቸውና ከመካከላቸው የ4ቱ ህይወት ወዲያውኑ ማለፉን ዘጋቢያችን ከስፍራው ካስተላለፈው ዜና ለመረዳት ተችሎአል።

የአላባ ህዝብ ለተቃውሞ በመውጣቱ ምክንያት የፊደራል ጸጥታ ሰራተኞች በቦታው ደርሰው ህዝቡን ለመበተን በከፈቱት ተኩስ የቆሰሉት በርካታ ሰዎች በአሁኑ ሰ ዓት በአዋሳ ሆስፒታል ውስጥ ህክምና እርዳታ እየተሰጣቸው መሆኑን የጠቀሰው ዘጋቢያችን፤ የወያኔ ፊደራል ፖሊሲ በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው በብዛ ተሰማርቶ እንደሚገኝ አስታውቆአል።

ወያኔ በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው ለዘመናት በሰላምና በፍቅር ተቻችሎ ይኖር የነበረውን ህዝብ በመለያየት በዘረጋው የአስተዳደር መዋቅር ቅር የተሰኙት የደቡብ ህዝቦች በተለያዩ ጊዜያቶች ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ ሲያቀርቡ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ከወያኔ ይሰጥ የነበረው ምላሽ ግን ፍጹም ፋሽስታዊ በሆነ ጭካኔ በጥይት መደብደብና ጸጥ ማሰኘት መሆኑ ተደጋግሞ መከሰቱ አይዘነጋም።

ባደወቾ ወረዳ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በተደጋጋሚ ለምርጫ እየተወዳደሩ ያሉበት ወረዳ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ፌደራል ሃይል በስፍራው ገብቶ ለማረጋጋት ቢጥርም ከፍተኛ የጸጥታ ችግር እንዳለና ነዋሪው አከባቢውን ጥሎ ወደ አጎራባች ወረዳዎች እየተሰደደ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመልክቷል። አራቱን ሰዎች በጥይት መትተው የገደሉት የሃዲያ ዞን ፖሊሶች መሆናቸውንም ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ ሰዎች ለኢሳት ምንጭ እንደተናገሩ ኢሳት በትናንትናው ዕለት ዜና እወጃው ዘግቦታል።

በ1995 አመተምህረት በአዋሳ ላይ በ1996 ደግሞ በጋምቤላ ላይ የተፈጸመው አስቃቂ ጭፍጨፋ በክልሉ የሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦች አንስተውት ከነበረው አስተዳደራዊ ክልሎች ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይታወቃል።

ወያኔ በተፈጥሮ ለምና ድንግል የሆነውን ወልቃይት ጠገዴን፤ ሴቲት ሁሜራና ፤ እንዲሁም በወሎ ክፍለሃገር ስር ይተዳደሩ የነበሩትን ቆቦንና ራያን የመሳሰሉትን ቦታዎች በሃይል ወደ ትግራይ ክልል እንዲዛወር እንዳደረገ፤ በምስራቅ ኢትዮጵያ የሱማሌንና ኦሮሞ ብሄሮችን የሚያዋስኑ ቦታዎች እንዲሁ ለግጭትና ለ እርስ በርስ ጦርቶች ሚቹ ምክንያት እንዲሆኑ እንዳደረገ ተደጋግሞ ሲዘገብ መቆየቱ አይዘነጋም።

## በትግራይ ህዝብና በህወሃት ሥም በህዝባችን ላይ ወንጀል እየፈጸመ ያለው የመለስ ዜናዊ ቡድን በትግራይ ህዝብ በአደባበይ ተወገዘ

ባለፈው ሳምንት በመኪና አደጋ ህይወታቸውን ያጡትና በከባድ ሁኔታ የቆሰሉት የነባር ህወሀት ታጋይ አርቲስቶች ጉዳይ፤ የትግራይን ህዝብ ክፉኛ እንዳስቆጣ የቀድሞ የህወሃት አመራር አባል የነበሩ አቶ አስገደ ገብረሥላሴ መግለጻቸውን ኢሳት ዘገበ።

ታጋይ አርቲስቶቹ በሱዳን ዝግጅታቸውን ለማቅረብ በመስቀል ዋዜማ በአሮጌ አውቶቡስ ከመቀሌ ተነስተው ጉዞ ቢጀምሩም፤ በስተደቡብ 200 ያህል ኪሎ ሜትር ከተጓዙ በሁዋላ ቆቦ አካባቢ ሲደርሱ አውቶቡሱ ተገልብጡ 10 ታጋዮች ወዲያው መሞታቸውና 17ት ታጋዮች ደግሞ በከባድ ሁኔታ መቁሰላቸው ይታወቃል።

“ለዘግናኙ የመኪና አደጋ እልቂት ተጠያቂው ማነው?”በሚል ርዕስ አቶ አስገደ ባቀረቡት ዕሁፍ እንደጠቆሙት፤ የአርቲስቶቹ አደጋና ከተሰማ ጀምሮ የመቀሌ ነዋሪ፡-”ሌቦች! ስስታሞች! የሄሊኮፕተር ላለመክፈል ብለው አስጨረሷቸው! ሌላው ቢቀር ለ 26 ሰው እኮ ሶስት ኮብራ መኪና ይበቃ ነበር። ለራሳቸውማ ቢሆን ኖሮ ለአንድ ሰው- አንድ አውሮፕላን ሲያንቀሳቅሱ እናውቃቸዋለን” በማለት ቁጣውን በስርዓቱ ሹመኞች ላይ እያሰማ ይገኛል። እንደ አቶ አስገደ ገለፃ፤ይህ ቁጣ እየተንፀባረቀ ያለው፤ በነዋሪ፣ በነጋዴው፣ በመንግስት ሠራተኛውና በህወሀት አባላት ጭምር ነበር።

የሟቾቹ አስከሬን ምሽት ላይ ሚላኖ ሆቴል እንደደረሰ የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ከሆኑት አንዱ አቶ ቴወድሮስ ሀጎስ ማልቀሳቸውን የጠቀሱት አቶ አስገደ፤ አጠገባቸው የነበሩ ወጣቶችና ሴቶች ግን፡- ”አስመሳዮች! እናንተን ማን ያምናችሁዋል? ማታ ማታ ለአንድ ጠርሙስ ብሉ ሌብል ውስኪ ከ 6 ሺህ እስከ 10 ሺህ ብር እያፈሰሳችሁ ወንድሞቻችንን በ አሮጌ መኪና ልካችሁ አስጨረሳችሁዋቸው! አሁን የምታለቅሱት ማን ያምነናል ብላችሁ ነው?” ሲሉ እንደነበር ጠቁመዋል።

“ከዚህም ባሻገር ወጣቶቹ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሂሳደቡ ይደመጡ ነበር” ያሉት አቶ አስገደ፤ “ወጣቶቹ ያመረሩበት ነገር ቢኖር ነው እንጂ፤ እንደዚህ እየጮኹ በህወሀት ባለስልጣኖች ፊት ተሳድበው አያውቁም ነበር” ብለዋል።

እንዲሁም አስከሬኑ ከሚላኖ ሆቴል ተነስቶ አይደር ሆስፒታል ሲደርስም በስፍራው የተሰበሰበው በርካታ ህዝብ ቁጭት በተሞላበት ሀዘን ቁጣውንን ስድቡን በህወሀት ሹመኞች ላይ ሲያወርደው መሰማቱን አቶ አስገደ በፅሁፋቸው ገልጸዋል።

በተለይ የ አስከሬኑ ሽኝት እንደተጠናቀቀ በወያኔ ተሹሞት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጳጳስ አቡነ ጳውሎስ ከተናገሩ በሁዋላ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አባይ ወልዱና የመለስ ዜናዊ የደህንነት አማካሪ ፀጋይ በርሄ ንግግር ማድረግ ሲጀምሩ አብዛኛው ህዝብ በቁጣ ስነ ስርዓቱን አቋርጦ መመለሱንና በስፍራው የነበሩ የህወሀት አመራሮች አስኪደነግጡ ድረስ ከፍ ያለ ተቃውሞ መሰማቱን አቶ አስገደ አመልክተዋል።

ልክ ሹመኞቹ መናገር ሲጀምሩ አንዳንድ ሰዎች ጮኸ ብለው፡- ”አታጭበርብሩን! ራሳችሁ ከገዳላችሁዋቸው በሁዋላ ቀብራቸውን ወደ ፖለቲካ ማራመጃነት በመቀየር አታጭበርብሩን!” ማለታቸውን የጠቀሱት አቶ አስገደ፤ ይሄ ተቃውሞ ኪዚያም፤ ከዚህም ሂስተጋባ የሰሙ የህወሀት አመራሮች በሙሉ በድንጋጤ አንገታቸውን መድፋታቸውን ገልፀዋል።

እስከዛሬ ድረስ በመቀሌ ኤፍ .ኤም ራዲዮ ስርጭት፤ ተመሣሳይ የህዝብ ቁጣ እየተስተጋባ መሆኑንም አቶ አስገደ ሳይጠቁሙ አላለፉም። ታጋይ አርቲስት ኢያሱ በርሄ በተንኮል እንደተገደለ የሚያረጋግጡ መረጃዎች አፈትልከው እንደወጡ መዘገቡ ይታወሳል።

ህወሃት የትግራይን ህዝብ እያስገደለና ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ እያጋጨ የትግራይን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርገው ጥረግ ከጊዘ ወደጊዜ ከፍተኛ አጣብቅኝ ውስጥ እየገባ እንደመጣ በርካታ የትግራይ ተወላጆች ይናገራሉ።

## በሎንዶንና በኦስሎ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚዎችን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተመሳሳይ ዜና በሎንዶን በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የአገራችንን የነጻነት አርማ የሆነውን ባንድራችንን ሲያዋርድ የኖረው መለስ ዜናዊና ድርጅቱ ህወሃት፤ ዛሬ ድርሶ የባንድራ አፍቃሪ ለመምሰል የባንድራ ቀን እንዲከበር አዋጅ ከማውጣት አልፎ በባንድራ ቀን ከቤታችሁ ደጃፍ ባንድራ አላውለበለባችሁም በሚል ሰበብ በፖለቲካ ባላንጣነት የሚፈርጀውን ወገን በገንዘብና በእስር መቅጣት መጀመሩ እንደሚያንገበግባቸው ገልጸው፤ ተቃውሞዋቸውን ለመግለጽ ወያኔ በባንድራችን ላይ የለጠፋትን የአንባሽ ምስል በመቀስ በማውጣት በዕሳት እንዳጋዩት ለማወቅ ተችሎአል።

የሎንዶኑን ሰልፍ ያዘጋጀው የኢትዮጵያዊያን ስብስብ አስተባባሪ በ ዕለቱ ባደረጉት ንግግር የመለስ ዜናዊ ሽብርተኛ አገዛዝ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን በደልና ሰቆቃ ለማስቆም ሁላችንም ጸንተን ልንታገለው እንደሚገባ ገልጸው ይህ ግፈኛ አገዛዝ ተገርስሦ በምትኩ ህዝብ ያስተዳድረኛል ብሎ የሚመርጠው የመንግሥት ሥርዓት በአገራችን እስኪገነባ ድረስ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም ኢትጵያዊ የበኩሉን አስተዋጾ እንዲያደረግ ጥሪ በማቅረብና በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ምክንያት ጥቃት ላይ የወደቁትን ዜጎቻችንን ቤተሰቦች ለመርዳት እንደሚተባበሩ በመግለጽ ለዕለቱ የተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ተበትኖአል።

በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የሚያደርጉት ሰላማዊ ስልፍ በሌሎች የአውሮጳ፤ የሰሜን አሜሪካና አውስትራሊያ የተለያዩ ከተሞች በተከታታይ እንደሚደረግ እየደረሱን ያሉ መረጃዎች ያመለክታሉ።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። <u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org